# በድንቁርና ላይ፤ ወሮወሸባ እንበል!

*ታደለ መኩሪያ*

የ 2005 ዓመተ ምህረት የትምህርት ዘመን በመስከረም ወር እንደሚጀመር ይታወቃል። ስለትምህርቱም አሰጣጥ ሕዝቡ እንደሚሳተፍበት ተስፋ አለኝ። በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ ንግሥም ሆነ በደርግ አስተዳደር ሥረዓተ ትምህርቱ በባለሞያዎች ቢዘጋጅም ሕዝቡን ያሣተፈ ባለመሆኑ ተቃውሞ ይቅርብበት ነበር። በወያኔ መንግሥት ከነጭራሹ ሥረዓተ ትምህርቱ በባለሞያዎች መዘጋጀቱ ቀርቶ የፖለቲካ ውሳኔ ሆነ።

ለምሳሌ ወያኔ 1983 ዓ ም ሥልጣን ሲቆጣጠር ቋንቋን መሠረት ያደረገ ክልል ፈጥሮ በዚያው መልክ ሥረዓተ ትምህርቱን አዋቀረ። ይህ አይነት አሰራር ኢጣሊያን 1928 ዓመተ ምህረት በወረረችን ጊዜ የተጠቀመችበት ዘዴ ነበር። በኤርትራም ለሰልሳ ዓመታት ተጠቅመበታለች። ዜጎች ከፍተኛ ትምህርት እንዳያገኙ በቋንቋቸው ይማሩ በሚል ስም በስድስተኛ ክፍል ደረጃ ተወስነው እንዲቀሩ ተደርጎ ነበር ። ዛሬም የወያኔ አስተዳደር የቅኝ ገዢዎች ቅጂ የሆነውን ሥረዓተ ትምህርት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተፈፃሚ ሲያደርገው እናያለን። በእርግጥ ልጆች በአፍ መፍቻቸው ቋንቋ መማራቸው ችግር አልነበረውም። ችግሩ ሕዝቡ በነፃነት ሳይመክርበት ሥረዓተ ትምህርቱ ወጤታማነቱ ሳይጠና መጽሐፍቶች ሳይዘጋጁ መምህራን ሳይሰለጥኑ በፖለቲካ ካድሬዎች ትምህርት ሊስፋፋ አይችልም። ይበልጥ ድንቁርና ይስፋፋል እንጂ።

የበለጸጉ አገሮች የትምህርትን ሥራ በቀላሉ የሚያዩት አይደለም። ለማንኛውም ችግር መፍቻ ቁልፍ መሆንን አምነው በየአካባቢው ስለአካባቢው ያካተተ ሥረዓተ ትምህርት ያዘጋጃሉ። ይህን አስመልክቶ በሕዝብ የሚመረጡ ወኮሎች በየደረጃው ይኖራሉ። (School Trustees) ይባላሉ። እነዚህ የሕዝብ ተወካዮች በአካባቢያቸው በሚገኙት ትምህርት ቤቶች የሚከናወነውን ሥረዓተ ትምህርት ይከታተላሉ፤ ሕብረተሰቡ እንዲያውቅ ያደርጋሉ። መገናኛ ብዙሃን ይተቹበታል፤ ወላጆች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፤ የመለዓተ ሕዝቡን ድጋፍ ያገኘው ያካባቢው ሥረዓተ ትምህርት ይሆናል። በአካባቢ የጀመረው በወረዳ፣በአውራጃ በክፍለ ሃገር እያለ ለሃገሪቱ አንድ የዕውቀት ዊቂያኖስ ይፈጥራል። የሚሻሻል ካለ በየጊዜው ይሻሻላል። በአካባቢው የትምህርት ተወካዮች ፣የወረዳው ትምህርት ቤት ጽፈት ቤት፣ የያንደንዱ ትምህርት ቤት አስተዳደር፣ መምህራን፣ የመምህራን ማሕበር፣ የተማሪዎችና የወላጆች ተወካዮች በአጠቃላይ ዜጎች ተባብረው የትምህርቱን ሥራ ወደፊት ያራምዱሉ። በዚህ ዓይነት፣የተዋቀረ ሥረዓተ ትምህርት ለአዲስ ግኝት ለሕብረተሰቡ እድገት ለችግሮች መፍቻ መንገድ ሆኖ በዕውቀት የገፉ ሕዝቦች ተደላድለውና ተደላቀው እንዲኖሩ ረድቷቸዋል።

እላይ የጠቀስኩት አሠራር ተግባራዊ እንዲሆን ሕዝቦች ያለመሸማቀቅ ሐሣባቸውን በነፃነት የሚገልጽበት ሥረዓት መኖር አለበት ። ይህ ሥረዓት 'ዲሞክራሲ' የሚባለው ነው። የማንኛው ዜጋ መብት የተጠበቀበት ስለሃገሩ ያለፍረሃት መግለጽ የሚችልበት ነው። አእምሮው ክፍት ሆኖ ሊያስብ ሊጽፍ ሊያስተምር ሊማር የሚያስችለው ሥረዓት ነው። በእርግጥ አብዛኛው ሕዝባችን ያልተማረ ቢሆንም እነዚህን መሠረታዊ መብቶቹን ገፎ ትምህርት አስፋፋለሁ ማለት በትውልድ፣ በሃገር፣ በሐብትም መጫወት ነው።

በየጊዜው ሃገራችንን የመሩ መሪዎችም ቢሆኑ የትምህርቱ ሥራ ውጤታማ እንደልሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ችግሩን በሃገር ደረጃ ከመፍታት ይልቅ በራሳቸው ቤተሰብ ዙሪያ ብቻ ያተኩራሉ። ለምሳሌ ልጆቻቸውን በውጭ ሃገር ልከው ያስተምራሉ፣ ቤተሰባቸው ሆነ ራሳቸው ሲታመሙ ከውጭ አገር ሄደው ይታከማሉ። ለሕክምናም ሆነ ለትምህርት ለቤተሰባቸው የሚያፈሱት መዋለ ንዋይ የሃገር ሐብት ነው። በሃገር ቤት ሆስፒታልና ትምህርት ቤት ይሠራል። የሃገራችን ሐብተሞች ቢሆኑ ከመሪዎቹ የተለዩ አይደሉም።ለምሳሌ ጃፓኖችን በሥልጣኔቸው እናደንቃለን፤ ይህ ያለመሰዋዕትነት የተገኘ አይደለም። የሃገሪቱ ሐብታሞች ልጆቻቸውን ከውጪ አገር ልኮ ከማስተማር ይልቅ ዕውቀቱ ወደሃገራቸው እንዲፈስ የሃገራቸው ሕዝብ በእኩልነት ትምህርት እንዲገበይ

ጠንክረው ሠርተዋል። ከመንግሥት ጋር በመተባበር  የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲዎች ገንብተዋል።

ይህ እንደለ ሆኖ በሃገራችን ትምህርት ቤቶች ቢገነቡም፣ ተማሪዎችና መምህራን በተቋሞቹ ውስጥ ቢገኙም የመማርና የማስተማር ነፃነት የላቸውም። በአሁኑ ጊዜ በሃገራችን ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ተከፍተዋል፤የሚማሩት ተማሪዎች የሚያስተምሩት መምህራን፤ከምር ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ ናቸው ወይ? (An academic freedom) የሚባለው ለእነርሱ ይሰራል ወይ? መልሱን ለእነርሱ  ልተወው። ከአንድ ዩኒቨርሲቲ የተመረቀ ወጣት ለራሱ ሠርቶ መኖር ይችላል? የዩኒቨርሲቲዎቹ ፕሮፌሰሮች በዓለም ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች ገብተው ተምረው አንቱ የተባሉ ዕውቀትን የተላበሱ፣ በእርግጥ  የአእምሮ ነፃነት አላቸው? ከሌላቸውስ? እንደሌላቸው  እያወቁ መምህር ነኝ ማለት ይቻላል? ተማሪውም የተማረውን ትምህርት ተጠቅሞ ሕይወቱን  በሃገር ውስጥ መለወጥ  ካልቻለ፣ ለባርነት ወደ አረብ ሃገር ከኮበለለ የትምህርቱ ሥራ ችግር አለው ማለት ነው። መምህሩም  ሥረዓተ ትምህርቱም  የተማሪውን የዕውቀት  አድማስ ካላሰፉ አስተማርኩ ማለቱ ፋይዳው ምኑ ላይ ነው? በሞያው የጠለቀ ዕውቀትና ፍቅር ያለው መምህር ያንን አያደርግም።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ወጣት ተማሪዎችና መምህራን ዘመኑ ያሰገኘውን ዕደ ጥበብ ተጠቅመው በዕውቀት ፋና ሲኖግዱ በኢትዮጵያ ግን ትምህርትን የፖለቲካ መሣሪያ በማድረግ ወደ ድንቁርና ጎዳና እየተነጎደ ነው። መገናኛ ብዙሃን በኢትየጵያ አገልግሎት እንደይሰጡ መደረጉ ጥሩ ምሳሌ ነው። በዚች ሰዓት የዓለም ወጣቶችና መምህራን  internet, face book. Twitter  youtube, video, television, radio እየተጠቀሙ ድንቁርናን እየተዋጉ ይገኛሉ። ( On line) በሚባለው መገናኛ ብዙሃን አንድ ፕሮፌሰር አዲስ አበባ ተቀምጦ ጋንቤላ ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ትምህርት ሊሰጥ ይችላል። አሜሪካ ያለ ኢትዮጵያዊ የቀዶ ጥገና ዶክተር ጥቁር አንበሳ ካለው ዶክተር ጋር (On line) ተረዳድተው በሽተኛውን ሊያክሙ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች መምህራን በአጠቃላይ ሕዝብ የተነፈገው ይህንን ነው። ሕዝቡስ አይወቅ ተማሪዎችና መምህራን ይህንን አያውቁት ይሆን? መልሱን ለእነርሱ ልተወው።

ስለዚህ በአንድነት በ2005 ዓ መተ ምህረት የትምህርት ዘመን፤ ለልጅ ልጆቻችን የሚጠቅም፣ ዘላቂነት ያለው ፣ በራሳቸው ተማምነው፣ የፈጠራ ችሎታቸወን አዳብረው፤  አካባቢያችውን ለውጠው ፤ለማበልጸግ  የሚረዳቸውን ሥረዓተ ትምህርት ቀርጸን፤ በድንቁርናና ኋላ ቀርነት ከርሰ መቃብር ላይ ቆመን ፤ ወሮወሸባዬ ተሳካ አላማዬ እንደምንል ቅጣት  ያህል ጥርጥር የለኝም።